# አሊሞኒ በዲሲ

*ኣሊሞኒ* (በተጨማሪም ለፈቱት የትዳር አጋር የሚከፈል ክፍያ ተብሎ ይጠራል) ማለት ለፈቱት ወይ በህግ ለተለያዩት የትዳር አጋር የሚከፍሉት የፋይናንስ ድጋፍ ነው። ለተወሰነ ግዜ ወይ ፍርድ ቤት ትእዛዙን እስኪቀይር የሚሰጥ ሊሆን ይችላል። ከሁለቱም አንዱ አሊሞኒ መጠየቅ ይችላል።

*ግዝያዊ ኣሊሞኒ* (በተጨማሪም ፒንደንቲ ሊት አሊሞኒ ተብሎ ይጠራል) የሚሰጠው የፍቺ ጉዳዩ በሂደት ላይ እያለና የፍርድ ሂደቱ እስኪጠናቀቅ አንደኛው ለማገዝ ነው። ፍቺው ሲጠናቀቅ ግዝያዊ አሊሞኒ ያቆማል እንዲሁም ፍርድ ቤቱ በቀጣይ ከፍቺ በኋላ አሊሞኒ እንዲከፈል ሊወስን ይችላል። አሊሞኒ እንዲሰጥ ከተወሰነ፣ የአበሉ መጠን ከግዝያዊ አሊሞኒ መጠን ሊለይ ይችላል።

የዚህ አሊሞኒ ዓላማ ‹‹ምክንያታዊና አስፈላጊ›› የሆነ ድጋፍ ለማቅረብ ነው። አሊሞኒ የሚጠይቀው ሰው የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያስፈልገውና ሌላኛው አጋር ይህን የገንዘብ ድጋፍ ማቅረብ እንደሚችል ማረጋገጥ አለበት።

ከሁለቱም አንዳቸው ከጠየቁ፣ ፍርድ ቤቱ ‹‹ፍትሀዊና ተገቢ ከሆነ›› አሊሞኒ እንዲከፈል ሊያደርግ ይችላል። ዳኛው በሁኔታዎ ላይ ያለውን ተዛማጅ ጉዳይ ይመለከታል። ሕጉ የሚከተሉት ነገሮች እንዲያካትቱ ያስቀምጣል፡

- አሊሞኒ የሚጠይቀው አካል ራሱን ወይ ራሷን የመደገፍ አቅም፡
- አሊሞኒ የምትጠይቀው/የሚጠይቀው ሰው ስራ ወይ ስልጠና የሚያገኝበትና ስራ የሚጀምርበት ሁኔታ፡
- በትዳር ግዜ የተቀመጠው የኑሮ ደረጃ፡
- የትዳር ርዝመት፡
- ወደ መለያየት ያመራው ሁኔታ፡
- የእያንዳንዱ አካል ዕድሜ፡
- የእያንዳንዱ አካል አካላዊና አእምሯዊ ሁኔታ፡
- አሊሞኒ የሚከፍለው አጋር ገቢ፣ ሊኖር እሚችል ገቢ፣ የከዚህ በፊት የህፃን ማሳደግያ ድጋፍ፣ ፋይናንሳዊ ሀላፊነት፣ የጡረታ ጥቅም የማግኘት መብትና ሌሎች ሁኔታዎችን ጨምሮ የራሱንና የሌላውን አካል መደገፍ የሚችልበት አቅም።

አሊሞኒ እየጠየቁ ወይ የአሊሞኒ ጥያቄ እየተቃወሙ ከሆነ ገቢዎንና ወጪዎን (በጀት) የሚያሳይ የሂሳብ መግለጫመመላት ይኖርቦታል።

**አሊሞኒ ከፈለግኩኝ ምን አደርጋለሁ?**

በፍቺ ወይ ሕጋዊ መለያየት ውስጥ ያሉ አካላት በግላቸው የአሊሞኒ ስምምነት ሊኖራቸው ወይ አሊሞኒ የሚያስፈልገው ሰው በፍቺ ወይ ሕጋዊ መለያየት ውስጥ አሊሞኒ እንዲከፈለው መጠየቅ ይችላል። እንዲሰረዝ ከተጠየቁና ሌላኛው አካል ይህን ከተቃወመ፣ ጉዳዩ በሂደት ላይ እያለ ጊዝያዊ አሊሞኒ የሚከፈሎት ሲሆን፤ ነገር ግን ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ አሊሞኒ አይከፈሎትም።

**አጋሬ በአበሉ ከኔ ጋር ካልተስማማስ?**

ፍርድ ቤቱ እንዲወስን መጠየቅ ይችላሉ፡ ፡

**አጋሬ አሊሞኒ ከፈለጉና እኔ ካልተስማማሁ ምን አደርጋለሁ?**

*በክስ* (ሕጋዊ መረጃ) ሂደት ላይ በዚህ እንደማይስማሙና አሊሞኒ መክፈል የሌለቦትን ምክንያት ለዳኛውና ፍርድ ቤት መንገር አለቦት፡ ፡ ዳኛውአሊሞኒ መክፈል እንዳለበት ወይ የሌለበት፣ ከተከፈለ መጠኑንና ለምን ያህል ግዜ በሚለውላይ ውሳኔ ይሰጣል፡ ፡

**በፍቺ ግዜ አሊሞኒ ካልጠየቅኩኝና አሁን እንደሚያስፈልገኝ ከወሰንኩስ?**

በፍቺ ወይ ሕጋዊ መለያየት ሂደት ውስጥ አሊሞኒ መጠየቅ አለቦት፡ ፡ ጉዳዮ ካለቀ በኋላ መጀመርያ ግዜ መጠየቅ አይችሉም::

**አሊሞኒ ለምን ያህል ግዜ ማግኘት እችላለሁ?**

እርስዎና አጋርዎ ከተስማሙለፈለጋችሁት ግዜ ያህል መሆን ይችላል፡ ፡ በዚህ ካልተስማሙ፣ ዳኛውአበሉ ግዝያዊ፣ ቋሚወይ ለሁኔታዎ አመቺ በሆነ መልኩ እንዲሰራ ሊወስኑ ይችላሉ፡ ፡

*ቋሚአሊምኒ* አንደኛውአካል እስኪሞት ወይ በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ለውጥ ወይ አካላቶቹ እስከ ተስማሙበት ይቆያል፡ ፡ *በጊዜ የተገደበ አሊምኒ* (በተጨማሪም *ዳግም ማገ ገምያ አሊምኒ* ተብሎ ይጠራል) በፍርድ ቤቱ ለታዘዘውግዜ ወይ አካላቶቹ ለተስማሙበት ግዜ፣ በአጠቃላይ የሚቀበሉት አጋር ራሳቸውን ለመቻል የስራ ልምድ ወይ ስልጠና እስኪያገኙ ይቆያል፡ ፡

**አሊሞኒ የምቀበል ከሆነና ዳግምባገባስ?**

አብዛኛውግዜ የአሊሞኒ ትእዛዝ ዳግምሲያገቡ ያቆማል፡ ፡ ይህ ትእዛዝ ይህን የመሳሰሉ ነገሮች ካላከተተ፣ እርስዎ ዳግምማግባቶ የቀድሞአጋሮ አሊሞኒ ለማቋረጥ ምክንያት አይሆንም፡ ፡

**የቀድሞአጋሬ የአሊሞኒ ክፍያ ካዘገዩስ?**

የፍርድ ቤት ትእዛዝ በመጣስ ፍርድ ቤት በመክሰስ እንዲያስፈፅምሎት መጠየቅ ይችላሉ፡ ፡

**ከፍቺ በኋላ አሊሞኒ ሊቀየር ይችላል ወይ?**

አዎ፣ በሁኔታዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ለውጥ ካለ፡ ፡ ለውጡን የሚጠይቀውአካል ትእዛዙን ለማሻሻል ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡ ፡ የሚከፍለውየቀድሞአጋር አቅምላይ ለውጥ ካለ ወይ ክፍያ በሚቀበለውሰውፍላጎት ላይ የፍላጎት ለውጥ ካለ ዳኛውአሊሞኒ ሊያሻሽል ይችላል። እርስዎና አጋርዎ በአበሉ ከተስማሙየሚፈርሙት ስምምነት ላይ አሊሞኒ መሻሻል ስለ መቻሉ መግለፅ አለበት።

**ከአሊሞኒ ግብር መክፈል አለብኝ?**

በአጠቃላይ፣ ፍርድ ቤቱ አሊሞኒ እንዲከፈሎት ከወሰነ ፤ ይህን አሊሞኒ በግብር ከፋይ ፎርሞ ላይ እንደገቢ መመዝገብ አለቦት። ከፋዩ ይህን አሊሞኒ ከገቢውወይ ከሚከፍለውግብር መቀነስ ይችላል። ነገር ግን፣ ግብር በዚህ መንገድ የማይከፈልበት ምክንያት አለ። የግብር ህጉ

እርስዎና አጋርዎ አሊሞኒ ለተቀባዩ ግብር እንደመይከፈልበት ወይ ከፋዩ እንደ ቅናሽ እንደማይቆጥረው በፅሁፍ ከተስማሙ ይፈቀዳል።

እርስዎና አጋርዎ ስለ አሊሞኒ የፅሁፍ ስምምነት ካሎትና፤ ነገር ግን እንደ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ካልገባ፣ የአሊሞኒ ስምምነቱ IRS ግብር ሊቀነስበት ከፈለጉ ስምምነቱ ደንብ ማክበር አለበት። የበለጠ መረጃ ለማግኘት የግብር ባለሙያ ማውራት አለቦት።

**አሊሞኒ እንዴት መጠየቅ እችላለሁ?**

ስለ ጉዳዮ ለጠበቃ ማማከር ወይ እራስዎት ማመልከት ይችላሉ። አስፈላጊ የሆኑትን የፍርድ ቤት የፅሁፍ ክስ በ www.dcbar.org/pleadings ወይ ዲሲ ላይ ማግኘት ይችላሉ። ከፍተኛው የቤተሰብ ፍርድ ቤት መቀበያ ማእከል (500 Indiana Avenue NW፣ room JM-540)፣ ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 8:30 a.m. እስከ 5:00 p.m ክፍት ነው።